# ሙስና - የፀረ ድህነት ትግሉ ፈተና

**እንዳልክ** 08-23-17

በነዳጅ ምርቷ ከአለም ስምንተኛ ደረጃ ላይ የምትገኘው ናይጄሪያ በአህጉረ አፍሪካ ሙስና ከተንሰራፋባቸው አገሮች ከቀዳሚዎች ተርታ የምትሰለፍ ናት። በተለይም በነዳጅ ሀብቷ የበለጸገችውን የኒጀር ዴልታ ግዛት የሚያስተዳድሩ ሹማምንት ስልጣን ላይ በወጡ ማግስት በአውሮፓና በአሜሪካ የተቀናጣ ቤትና መኪና ለመግዛት የሚያደርጉት ሩጫ ችግሩን እንደሚያባብሰው ከታላላቅ ሚዲያዎች በተደጋጋሚ የሚደመጥ ዜና ነው። ከነዳጅ ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ወደ አገሪቱ ካዝና ከመግባት ይልቅ ወደ ግለሰቦች ኪስ መግባቱ የደሀውን ዜጋ ኑሮ ፈታኝ አድርጎታል። በሙስና መንሰራፋት የተነሳ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የኤሌክትሪክ ብርሀን ሳያዩ በጨለማ እንዲኖሩ ተገድደዋል።

በእኛም አገር ሙስና እያቆጠቆጠ በመምጣቱ በርካታ ዜጎች ማግኘት የሚገባቸውን መብት እያጡ ነው። ከሰሞኑ በመንግስት የስራ ሀላፊነት ላይ የተመደቡ ግለሰቦች፣ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች እና ደላሎች "በመንግስት ገንዘብ ላይ ጉዳት አድርሰዋል" በሚል በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር እየዋሉ ነው። ተጠርጣሪዎቹ ከስኳር ኮርፖሬሽንና ከስኳር ፋብሪካዎች፣ ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት፣ የአዲስ አበባ እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ውስጥ ሀላፊነት የነበራቸው ሲሆኑ፤ በስራ ሂደት ከሚያገኟቸው ባለሀብቶችና ደላሎች ጋር በመመሳጠር በቢሊዮን በሚቆጠር ገንዘብ በማባከን በአገር እና በሕዝብ ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ለአገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አመላክቷል።

የተጣለባቸውን መንግስታዊ ሀላፊነት ወደጎን ብለው ለግል ጥቅማቸው ያልተገባ ገንዘብ እያግበሰበሱ የሚገኙ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ለማዋልና ሙስናን በቁርጠኝነት ለመታገል በመንግስት በኩል የተጀመረው ጥረት ይበል የሚያሰኝ ነው። አገራችን ባለፉት አመታት ተከታታይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እያስመዘገበች መገኘቷ ደስ የሚያሰኝን ጉዳይ ቢሆንም፤ ከዕድገቱ ጎን ለጎን እያቆጠቆጠ ያለው የሙስና ድርጊት የዕድገት ተስፋችንን እንዳያጨልመው መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ስለሆነም መንግስት ህብረተሰቡን ከጎኑ በማሰለፍ የፀረ-ሙስና ትግሉን በአዝማችነት መምራት ይጠበቅበታል።

ዜጎች ከዛሬ ነገ አገራችን ከድህነት ወጥታ፣ ተለውጣና አድጋ ኑሯችን ይሻሻላል በሚል የጣሉትን ተስፋ በዜሮ እንዳናባዛው ከመልካም ምግባር የወጡ ድርጊቶችን መከላከል ያስፈልጋል። አንዳንድ ስግብግቦች ለራሳቸው ጥቅም ብቻ በማሰብ ያልተገባ ሀብት እያከማቹ በገበያ ጤናማ ውድድር እንዳይኖር እና የዋጋ ውድነት እንዲፈጠር የሚያካሂዱት አሻጥር ቶሎ እልባት ካላገኘ በተራዘመ የጊዜ ሂደት ውስጥ አገር የከፋ አደጋ ውስጥ ትወድቃለች።

በአሁኑ ወቅት በአገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት በማድረስ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር እየዋሉ የሚገኙ ግለሰቦች ጉዳያቸው በፍጥነት ታይቶ በጥፋተኞች ላይ ተመጣጣኝ ቅጣት መተላለፍ ይኖርበታል። የግለሰቦቹን መያዝ ተከትሎ በተሰጠው መግለጫ እንደሰማነው ከፍርድ ቤት በወጣ የብርበራ ትዕዛዝ መሰረት በተጠርጣሪዎቹ ቤት ውስጥ በተደረገ ፍተሻ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር፣ ዶላርና የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተገኝቷል። ተጠርጣሪዎቹ ከመያዛቸው በፊትም ለረጅም ጊዜ የቆየ ክትትልና ማጣራት ሲደረግም እንደነበረ ሰምተናል። ስለዚህ በዚህ ወቅት የተደራጁ ማስረጃዎችንና በሂደት በሚካሄድ ተጨማሪ ምርመራ ማስረጃዎችን ቶሎ አደራጅቶ አፋጣኝ ውሳኔ ማሳለፍ በቀጣይ ሙስናን ለመታገል የሚደረገውን ጥረት ያፋጥነዋል።

ዜጎች በሚያደርሱት ጥቆማ መሰረት ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ አካላት ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት ካላገኙ በቀጣይ ጥቆማ የሚሰጥ አይገኝም። ስለዚህ የህዝቦች ተባባሪነት እንዲቀጥልና ትግሉ የጋራ እንዲሆን የሚሰጡትን ጥቆማዎች ማጣራትና ተመጣጣኝ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

መንግስት ድህነትን ከሚታገልበት አቅም ባልተናነሰ ሙስናን መታገል አለበት። ለዚህ ትግል ህብረተሰቡን ማሳተፍ ደግሞ የግድ ነው። እንደዚህ ካልሆነ ነገሩ ሁሉ ታጥቦ ጭቃ መሆኑ አይቀሬ ነው። በአንድ በኩል የኢኮኖሚውን አቅም ለማሳደግ ጥረት

ሲደረግ፤ በሌላ በኩል ለምዝበራ ከተጋለጠ ባለንበት እየረገጥን እንቀጥላለን። ስለዚህ ሙስናን ለመዋጋት የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።

በአሁኑ ወቅት ዜጎች ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት ያለእንግልትና ያለአድልኦ ማግኘት ፈታኝ እየሆነባቸው መጥቷል። የቀበሌ መታወቂያ ከማግኘት ጀምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት እየተቸገሩ እንደሆነ እየታየ ነው። ይህ መንገላታት ምንጩ በአግባቡ አገልግሎት መስጠት ያለበት አካል ከሚቆረጥለት ምንዳ ያለፈ ጥቅም ለማግኘት የመፈለጉ ምክንያት ነው። በቀላሉ የሚገኙ መዝገቦች የሉም እየተባለ ለአንድ ጉዳይ ያልተገባ ምልልስና እንግልት የደረሰበትን ቤት ይቁጠረው። ይህንን ነገር ዛሬ ካላስቆምነው ችግሩ ከተባባሰ በኋላ "ምነው እናቴ በእንቁላሉ ጊዜ በቀጣሽኝ" የሚለው ተረት ዓይነት እንዳይደርስብን ያልተገባ ጥቅም ፈላጊነትንና በህጋዊ አሰራር ጥላ ስር ተጠልለው የሚገኙ ህገ ወጥነቶችን መዋጋትን ዛሬ ነገ ሳንል አሁኑኑ መጀመር አለብን።

በዚህ ዓመት የተካሄደው የጥልቅ ተሃድሶም ይህንን በግልጽ አመላክቶናል። ኪራይ ሰብሳቢነት የስርዓቱ አደጋ እንደሆነ ተመላክቷል። ኪራይ ሰብሳቢነትን ሳናሸነሙነው ሌብነት እንደሆነ አውቀን ወደተጠናከረ ትግል ውስጥ መግባትና የፀረ ድህነት ትግሉን ፍሬያማ ለማድረግ መስራት ይኖርብናል። እንደአገር ለመቆም ሌብነትን መዋጋት ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። እንዲህ ካልሆነ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮቻችን ላይ የሚፈጠረው ቀውስ አስከፊ መሆኑ አይቀሬ ነው።

የሙስና ድርጊት የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ በብዙ አቅጣጫ የሚከሰት ነው። ድርጊቱ በአንድ አገር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያሳርፈው በትር ከባድነቱ መልሶ ለማገገም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ይሆናል። በፖለቲካ ምህዳር ዴሞክራሲ እንዳያብብ እንቅፋት ከመሆን ባለፈ የህግ የበላይነት እንዳይከበር መንገድ ይከፍታል። በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ተቋማትን እንዲመሩ ህዝባዊ አደራ የተጣለባቸው ግለሰቦች ስልጣናቸውን ከአግባብ ውጪ ተጠቅመው ለግል ጥቅማቸው ካዋሉት ህጋዊ መሰረቶችን እየናዱ እንደሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ሙስና እየተንሰራፋ ሲመጣ በህዝቦች መካከል አለመተማመን እየተፈጠረ ዜጎች በፖለቲካ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ የማድረግ ፍላጎታቸው ይመናመናል። የሙስና ተግባር ሳይራባና ሳይበዛ መቆጣጠር ካልተቻለ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት መስፈኑ፣ ጤናማ ውድድር መጥፋቱ እና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ማጣት መንሰራፋቱ አይቀርም።

እያንዳንዱ ሰው ባልተገባ መንገድ ጥቅም ባገኘ ቁጥር በተገቢው መንገድ ጥቅሙ ሊከበርለት የሚገባ ሰው ጥቅሙን ያጣል። በየትራፊክ መብራቱ በፕላስቲክ ኮዳ ማስቲሽ እና ቤንዚን እየሳቡ ናውዘው የምናያቸው፣ በየጎዳናው ወድቀው የምንመለከታቸው፣ የሚልሱት የሚቀምሱት አጥተው ጎዳና ለልመና የወጡ፣ የመኖሪያ ቤት ችግር ጠፍንጎ ይዟቸው በኪራይ ቤት ፍዳቸውን እያዩ የሚገኙ ቤተሰቦች፣ በትራፊክ አደጋ ህይወታቸውን፣ አካላቸውንና ንብረታቸውን የሚያጡ ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሙስና እንበለው ወይም የኪራይ ሰብሳቢነት ወይም የሌብነት ተግባር ሰለባዎች ናቸው።

ቤት ሰርቶ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የማስተላለፍ ሀላፊነት የተጣለበት ሀላፊነቱን ወደጎን በመተው ለራሱ የሚያግበሰብስ ከሆነ፣ ፍትህ ተጠምቶ ፍርድ ቤት የሚሄድ አካል ዳኞች ባገኙት ያልተገባ ጥቅም ፍትህ የሚዛባበት ከሆነ፣ መንገድ በጥራት መስራት ያለበት አካል ጥራቱን ያልጠበቀ መንገድ ሰርቶ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኪሳራ የሚያደርስ ከሆነ፣ የመንገድ ትራፊክ እንዲያስከብር ሀላፊነት ተሰጥቶት ባገኘው ያልተገባ ጥቅም የተነሳ የትራፊክ ደንብ ተጥሶ አደጋ እንዲደርስ የሚያደርግ ከሆነ፣ ወዘተ. የምንፈጽም ከሆነ የተሰጠንን ሀላፊነት ተጠቅመን አገራችንን በመግደል ላይ ነን ማለት ነው።

ሙስና ከግለሰብ ጀምሮ እስከ አገር ድረስ የከፋ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ያደርሳል። በሙስና አማካኝነት የሚደርስ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የአገር ሀብት በከፍተኛ ኪሳራ እንዲያሽቆለቁል ያደርጋል። የእኛ አገር ኢኮኖሚ ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ መነቃቃት ያሳየ ቢሆንም በአለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ እጅግ ዝቅተኛ ነው። ስለዚህ በዚህ ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ላይ ሌባ/ስርቆት ተጨምሮበት ነገሩ ሁሉ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆናል። የሙስና ተግባር ሲባባስ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ ይንራል። ትምህርት

ቤቶች፣ ሆስፒታል፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና መንገድን የመሳሰሉ መሰረተ ልማቶችን በጥራትና በበቂ መጠን ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ሁሉ መና ያስቀራል።

የህዝብንና የመንግስትን ሀብት ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ለግል ጥቅም ማዋል በገበያ ላይ አለመረጋጋትና የዋጋ ግሽበት ያስከትላል። በሙስና የተነሳ ሚዛናዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እየተመዘገበ በዜጎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል የመፍጠር ሂደቱን ገደል እንዳይከተው መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ከዚህም ባለፈ የስራ ላይ ስነምግባርን እያበላሸ ምርታማነትን እንዳይጎዳ ሙያና ሙያተኝነት ተከብሮ ያልተገባ ጥቅም የማግኘት እንቅስቃሴ መልክ እንዲይዝ መደረግ አለበት።

በመጨረሻም፤ የፌዴራል ዋና ኦዲተር እና የአዲስ አበባ ዋና ኦዲተር ያደረጉትን ምርመራ ተከትሎ ተጠርጣዎች በቁጥጥር ስር ከዋሉባቸው ተቋማት በተጨማሪ በሌሎች ተቋትም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ለኢኮኖሚው ስጋት የሆኑ አካላት ተገቢው ርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል። በተለይም በቢሊዮን ብር ደረጃ ግዢ የሚፈጽሙ ተቋማት፣ ዋናው ኦዲተር በተደጋጋሚ ችግር እንዳለባቸው የሚጠቁማቸው የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ወዘተ. ሀላፊዎች የተጣለባቸውን ሀላፊነት በታማኝነት ስለመወጣታቸውና በአገሪቱ ሀብት ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ መረጋገጥ ይኖርበታል። ህዝቡም መንግስት በሙስና ላይ እየወሰደ ያለውን ርምጃ በተመለከተ በቂ መረጃ እያገኘ የፀረ ሙስና ትግሉ አጋር ሀይል መሆን ይጠበቅበታል።